# ከእባብ እንቁላል የእርግብ ጫጩት የሚጠብቁ፣ ሳይነደፉ በፊት ይጠንቀቁ

ከሀይለ ልዑል ግርማ (ዋሽንግተን ዲሲ)

አዎን ከክፉ ነገር፣ ከአውቆ አጥፊ፣ ከለየለት ጠላት፣ ከከሃዲ ባንዳ መልካም ነገር፣ ጥሩ ነገር ይገኛል ብሎ መጠበቅ አንድም አላዋቂነት አሊያም ጅልነት ወይም ደግሞ አውቆ አጥፊነት ነው።

ሃያ አመት ሙሉ የወያኔን ጸረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ተግባርና ባህርይ ላየና ለሚያውቅ ሰው እንደው አንድ ቀን ተለውጦ ለህዝብ የሚጠቅም፣ ለአገር የሚበጅ ነገር ይሰራል ብሎ በዛሬው ጊዜ ማሰብ ከላይ ከተጠቀሰው አባባል ጋር ምንም ልዩነት የሌለው ነው። ሕዝባችን እየተራበ፣ እየሞተ፣ እየተሳደደ፣ እየተዋረደ፣ መሬቱ ለአረብና ለቻይና እየተሸጠ፣ ህዝብ ባገሩ ስደተኛ እየሆነ የኑሮው ውድነት መቋቋም እየተሳነው ሳለ የወያኔ ጆሌዎች አይናቸውን በጨው ታጥበው ወያኔ ኢትዮጵያን አሳደገ፣ ለወጠ፣ አሻሻለ እያለ ከበሮ የሚደልቁብንን ሆዳምና ባንዳ ደግሞ የቅሌት ሸማ እያከናነብናቸው እየታገልናቸው ካልሄድን በቀር ኢትዮጵያን የፈጠራት ወያኔ ነው ብለው የታሪክ መጽሀፍ ሊጽፉ ወይም ሊሰብኩን ይነሳሉና ክፉውን፣ አጥፊውን፣ ባንዳውን፣ ጠላትን ሁሉ በአንድ ሙቀጫ ከትቶ መውቀጥ ያስፈልጋል። በሀቅና በጽናት መታገል፣ ሚና መለየት የግድ ነው። ከወያኔ መወገን አለበለዚያ ከሕዝብ ጋር ለሕዝብ መቆም።

ወያኔ በገንዘብ ሀይል አማካሪ፣ ደጋፊ፣ ጉዳይ አስፈጻሚ እንደልቡ ስለሚያገኝ የራሱኑ ሰዎች አሰልጥኖ ከተቃዋሚው ጎራ በመቀላቀል ያዙኝ ልቀቁኝ የሚሉ "ተቃዋሚዎች" ሆነው መንገዱን ሁሉ "ጎድን፣ ጎድን" እያሉ መንገድ ያስለቅቃሉ። ሀገር ወዳዱን ስሙን በማጥፋት፣ ተስፋ የሚያስቆርጥ ዜና በማናፈስ የትግል ሀሞቱን ያፈሱታል። ወንበሩን ይዘው እንደልባቸው ወያኔን "እየሰደቡና እያወገዙ" በሌላ በኩል ደግሞ የውስጥ ስራቸውን እየሰሩ እድሜውን እያራዘሙ እነርሱም ሆዳቸውን እየሞሉ ይኖራሉ።

"የተቃዋሚ ህብረት፣ አንድነት፣ ጥምረት፣ ግንባር" እያሉ በጎሳና በዘር ድርጅት የሚያምኑ ሁሉ ስማቸውን በመቀያየር የትግል አቅጣጫ በማሳትና ግራ በማጋባት የሰው ሀይልና ጊዜ፣ ገንዘብና እውቀት በባዶ ሜዳ እንዲባክን ያደርጋሉ።

እነ ብርሃኑ ነጋ ቅንጅትን አፍርሰው አሜሪካ ከቀሩ በሁዋላ ስንት የትግል ዐመታት በከንቱ አሳለፉብን? ዲያስፖራውን የሌለ ነገርና ተስፋ በመንገር አዘናጉት፣ ከፋፈሉት ጊዜና ገንዘቡን ተጫወቱበት። ዛሬ ድግሞ የነከማል ገልቹ ተከታዮችን አምጥተውብን የኦነግን ባንዲራ ሲያሰወለውሉብንና የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዐላማ እንደ አሮጌ ጨርቅ ጣል ጣል እያደረጉ ሲያላግጡብን ሊሰቀጥጠን፣ ሊያንገበግበን፣ ሊያስቆጣን ይገባ ነበር። እነ ሰዬ አብርሃና ነጋሶ ጊዳዳ ደግሞ በጓሮ በር ገብተው አናት ላይ ቁጢጥ ብለው መድረክ፣ ዩዲጄ ተብለው ወያኔ ቁጥር ሁለትን ሲዘምሩልን የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር ይመስል አብረን የምንዘምር ደካሞች ምን እንባላለን? ምን ነካን? የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔን ለመጣል እንጂ መለስ ዜናዊን ለመቀየር ነው እንዴ ያንን ሁሉ መስዋዕትነት የከፈለውና የታገለው? ወንጀለኛና በደም የተጨማለቀውን ሁሉ መልሰን ለመሸከም የምንጓጓ ምን ነክቶን ነው? ዛሬ መድረኩን ሁሉ ያጣበቡት ሰዎች መለስን በሰዬ ተክተው ይህንን ዘረኛ ስርዐት ሊያቆዩብን ሲራወጡ ነቃ ብሎ ምንድነው እየተካሄደ ያለው? ማለት ተስኖን ሰዬ፣ ብርሃኑ፣ ፍስሀ፣ ካሳ፤ ገብሩ፣ ነጋሶ ተመልሰው እንዲሰለጥኑብን እየፈቀድን ነው። ወያኔ ቁጥር ሁለት ያለ መለስ ዜናዊ ፈቃድና ስምምነት የሚፈጸም ይመስላችሁዋል?

ከመሰላችሁ ተሳስታችሁዋል። በጥናትና በተቀነባበረ መንገድ የሚካሄድ ደባና ሴራ እየተዶለተብን ነው።

እነ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ (ታደሰ ቆርቾ) ቀደም ብሎ በሚሊቴሪ ውስጥ ሳለ በስውር ለሻእቢያና ለወያኔ ሲሰራ ኖሮ፤ ለሀያ አመት ደግሞ ከወያኔ ጋር እንዳልሰራ ሁሉ ዘሬ "አላሰራ አሉኝ" ብሎ የዩንቨርስቲውን ሽያጭ የትየሌሌ ብር ጭኜ ወጥቻለሁ እና በምናቋቁመው የሽግግር ምክር ቤት የመለስን መንግስት እንደው በወራቶች ውስጥ ገልብጠን እንጥለዋለን ብሎ ሲናገር አምኖ የሚቀበል ምሁር ተብዬ ምን ያህል የማሰብ ችሎታውን እንዳጣ መገንዘብ አያዳግትም። የዛሬው የሽግግር ካውንስል የነገው የሽግግር መንግስት ተሆኖ መለስን በሰዬ ለመተካት በሚደረገው ደባና ሴራ ባለማወቅ መጠቀሚያ ሊሆኑ የነበሩ ጥቂት ሰዎች ሁኔታውን አገናዝበውና አእምሮአቸውን ተጠቅመው ራሳቸውን ማግለላቸው እሰየው የሚያስብልና ከነገ ተጠያቂነትም ለመዳን በመቻላቸው መልካም ውሳኔና ምርጫ አድርገዋል። "ደርግ ይውደቅ እንጂ ያፈለገው ይምጣ" ተብሎ ለወያኔ አገር እንዲያጠፋ እድሉ የተሰጠበትን መጥፎ ጊዜ ብዙ ኢትዮጵያውያን በቁጭት የሚያስታውሱት ነው። አሁንም መለስ ይውረድ እንጂ ያፈለገው ይምጣ መባል የለበትም። የወያኔ ስርዓት ከነግሳንግሱ ከነዘረኛ አመለካከትና ከጎሳ ፖለቲካና አራማጆች ጋር መወገድ አለበት። ወንጀለኞች ለፍርድ መቅረብ አለባቸው። ገና ለገና አሜሪካ ደግፏቸዋል ተብሎ "በስኮላርሺፕ" ስም "እየሰለጠኑ" ያሉት እነ ሰዬ አብርሃና ብርቱካን ሚዴቅሳ፣ ቀደም ብለው ከተዘጋጁት እነ ብርሃኑ ነጋ፣ ከማል ገልቹ፣ ፍስሐ እሸቱ፣ የደርጉ ካሳ ከበደ፣ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ፣ ወዘተ.. ግሳንግሳቸውን ይዘው አዲስ አበባ ሊገቡ በራሳቸው "ባህታውያን" ትንቢት እያስነገሩ ነው። "የቡርቃ ዝምታ" ደራሲ ተስፋዬ ገብረአብ "ወፏ" ነግራው ይሆን በዚህን ጊዜ የሽግግር መንግስት በዚህ ወር ድግሞ መለስ ስልጣን ይለቃል ብሎ የጻፈው? ወገን ከኢ/ያ ሕዝብ ጀርባ የሚደገሰውን የጥፋት ድግስ ለመቋደስ ያሰፈሰፈው ሁሉ መጋለጥ አለበት።

ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ወያኔ በሚከተለው የዘረኝነት ፖሊሲ ከበላይ በመጣ ትእዛዝ በደቡብ ኢ/ያ የሚኖሩ አማርኛ ተናጋሪዎች አርሶ አደሮች ከነቤተሰቦቻቸው ወደ ክልላቸው እንዲመለሱ ተብሎ ላካባቢው ሹማምንት መመሪያ ተላልፎ እነርሱም ያንን ተግባራዊ ለማድረግ "ከሰሜን የመጣህ ወደ ክልልህ በማለት" ካለሙት፣ ሀብት ንብረት ካፈሩበት፣ ልጆች ከወለዱበት መንደር እያሰቃዩ ማባረር ሲጀምሩ በወቅቱ ይህንን አስደንጋጭና አሳዛኝ ሁኔታ በማጋለጡ በኩል የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የኢትዮጵያዊነቱን ግዳጅ ለመወጣት የሚችለውን ሁሉ በማድረጉ መፈናቀሉ በመላው ኢትዮጵያ እንዲታወቅና ህዝብ ተረባርቦ ድርጊቱን እንዲያስቆም፣ ተፈናቃዮችም እርዳታ አግኝተው መብታቸው ተጠብቆ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ጩኸት አሰምቷል፣ ታግሏል። መኢአድ የዜግነት መብታቸው ተገፏል እና ይከበር ሲል በውጭ ያሉ ደግሞ ዜናውን ተቀብለው "አማራ ተጠቃ፣ የአማራ ድርጅት መቋቋም አለበት" አሉ። ዜናው ሁሉ የአማራ ድርጅት መቋቋም ሆነ። ታዲያ እነ ሰዬ፣ ፍስሀ እሸቱና ብርሃኑ ነጋ እያቋቋሙ ያሉት የሽግግር መንግስት አካል የጎደለው አማራን የሚወክል ድርጅት ነበር። አሁን የተፈናቃዮች ሁኔታው በፈጠረውና በንዴትም በስሜታዊነትም የአማራ ድርጅት ይመስረት መባሉና "ሞረሽ" መገኘቱ ጮቤ አስረገጧቸው የድጋፍ መግለጫ ከነከማል ገልቹ ኦነግ ሁሉ ተሰጠ። የወያኔ ደጋፊዎችና አባሎች ሁሉ አማራው ተፈናቀለ ተባረረ እያሉ ማናፈስ ጀመሩ። እነ ኢሳት ቴሌቪዥን ያማራውን ጉዳይ ያራገቡበት መንገድ እና ዝግጅቶች ሁሉ የሚያመሩት የአማራ ድርጅት እንዲቋቋም ነው። ለምን? አማራው በስሜት የአማራ ድርጅት እንዲያቋቁም የሚመኙትና ያልተሳካላቸው ጉዳይ ስለነበር ነው። አማራው በኢትዮጵያዊነቱ እንጂ በዘር አልደራጅም ብሎ በመጽናቱ ኢትዮጵያዊነቱ ያንገበግባቸዋል። የጎሳ ፌዴራሊዝም ነውና ግባቸው "ዲሞክራሲ" ሰፈነ ለማለት እንደ ኦነግና ሌሎቹ ሁሉ የአማራ ድርጅት አባላቸው እንዲሆን ይፈልጋሉና።

የለም የዘር ድርጅት መቋቋም የለበትም፣ በኢትዮጵያዊነት መደራጀት፣ ለብሄራዊ አላማ መታገል ነው የሚያዋጣው የሚሉትን እርጉም ውጉዝ ተብለው ተወገዙ። የነሰዬ ደጋፊዎች ዛሬ የአማራ ተቆርቋሪ ሆነው ማነው ሞረሽን የሚነካው? ማለት ጀመሩ። ለኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ለተፈናቀለው አማራ መፍትሄው ግን ይህ አይደለም።

በዚህ አይነት ሁሉም በየዘሩ ከተሰባሰበ፣ ከተደራጀ ማነው ለኢትዮጵያ የሚታገለው? ማንም! የሚፈለገው ይሄ ነው። የወያኔ ዐላማ ተሳካ ማለት ነው። ጥቂት ሰዎች በአማራው ላይ በሚደርሰው ግፍና መከራ አዝነውና ተቆጭተው በስሜታዊነት ጥቃት የተከላከሉ መስሏቸው የገቡበት ሲሆን፣ የዳግማዊ ሴራ ሰዎች ደግሞ ለሚፈልጉት ዐላማ መጠቀሚያ ይበጀናል በማለት ትላንት አማራውን ምን ሲሉ እንዳልነበር ሁሉ ዛሬ ተሽቀዳድመው አብዛኞቹ መስራች አባሎች የሆኑትና የተሰገሰጉት የነሰዬ ደጋፊዎችና የ"በቃ" ሰዎች ናቸው። እነ አምባሳደር እምሩ ዘለቀ መኖራቸው የጠቀመው በስማቸው ታዋቂነት ብቻ ነው። ይህን አጀማመሩ አስፈላጊና መልካም የሚመስለውን ወደፊት ግን እንደነ ኦነግ መጫወቻ የሚሆን ድርጅት መመስረትም፣ ማቋቋምም፣ የጎሳ ድርጅትን እያወገዙ ከጉልበት ድረስ ተነክሮ መግባት ከአደገኛነቱ ባሻገር ለመውጣት ሲፈለግ ደግሞ አንገት ድረስ ሰምጦ ይሆንና ጉዳቱና ጥፋቱ ቀላል አይሆንም። ብዙ ጥፋት ሳይጠፋና ለነሰዬ አብርሃ መጫወቻ ሳይኮን በፊት መከላከል፣ የዘር ማጽዳትን ወንጀል ማስቆም የሚቻለው በኢትዮጵያዊነት ሲቆምና የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሀላፊነትና ግዳጅ ሲኮን ብቻ ነው።

የአማራውን፣ የአፋሩን፣ የወላይታውን፣ የኦሮሞውን ወዘተ… ጥቃት ለመከላከል ከኢትዮጵያዊነት በላይ ምንም ነገር የለም። አማራውን እኮ የሚያጠቁት በኢትዮጵያዊነቱ ብቻ ነው። ሌላውንም እንደዚያው። ስለዚህ በጎሳና በዘር መደራጀት ለአንዱ ክፍል ወንጀል ለሌላው ትክክል እንዴት ሊሆን ይችላል? ነገ በየሰላማዊ ሰልፉ፣ በየመንግስታት ደጅ በጎሳና በዘራችን ስም ተኮልኩለን እየጮኽን መፍትሄ ልናገኝ ነው? ጽድቁ ቀርቶ በውል በኮነነኝ አለ ያገሬ ሰው።

በማጠቃለዬም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም ነገር ሳያውቅ፣ ዋሽንግተን ዲሲ የአገር መግደያ መርዝ ተቀምሞ፣ ተፈጭቶ፣ ተቦክቶና ተጋጋሮ ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ የታቀደውን ዳግማዊ ሴራ በንቃት መጠበቅና መታገል ቀላል ሆኖ ሳለ፤ አገር ቤት ከገባ በሁዋላ ግን እንደ ባለጌ ታዛይ ከጀርባ አልወርድም እንደሚል ታውቆ "መለስ ከተቀየረ" ምናገባን በሚል የማዘናጊያ መረጃ የተወናበዳችሁ የተሳሳታችሁ ሁሉ አስባችሁ ራሳችሁን ከሴረኛው ቡድን በማግለል፣ ከቻላችሁ ከእውነተኛ ለውጥ ከሚያመጡትና በአገር ቤት መሰረት ካላቸው ጋር መታገል፤ ካልቻላችሁ ደግሞ አርፋችሁ ትቀመጡ ዘንድ እያሳሰብኩ እምቢም ካላችሁ ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ የሚባለው እንዳይደርስባችሁ ውርድ ከራሴ ብያለሁ። በሌላ ርእስ እስክመለስ ቸር ያሰንብተን።

የዳግም ታላቁ ሴራ በሀቀኛ የኢ/ያ ልጆች ትግል ይከሽፋል!

የጎሳና የዘር ድርጅት ይከስማል!

ኢትዮጵያዊነት ያብባል!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

ሚያዝያ 10 ቀን 2004